

የካቲት ፳፭ ቀን ፪፻፫ ዓ.ም (የካቲት 25፣ 2003)
March 4, 2011

# ከታሪክ ማኀደር

ባሹ ገመዳ

በቅርቡ አንድ ዘመዴ የአስመሣዩን የወያኔ "የቀይ ሽብር ሙዜየም" ለመጎብኘት በመሄድ "አደራ መቼም እንዳይደገም!!" በሚል ርዕስ የተከተበውን ልዩ እትም መጽሔት ግንቦት ፪፻፩ ዓ.ም (2001) ልኮልኛል። በዚህም መጽሔት ውስጥ ደርግ "የፍጌል ወጠጤ" ብሎ ሊያቅራራባቸው የፈለጋቸውን ታጋዮች ፎቶ በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም (1969) በዘመኑ በነበሩ





ተባባሪዎቹ (የኋለኛ ተጠላቶቹ) ትብብር አሳትሞ አዲስ አበባና አካባቢው እንዲሁም በየጠቅላይ ግዛቱ በመበተን በየግድግዳው ለጥፎ እንደነበር ብዙዎቻችን አናውቃለን። ይህ መጽሔት የሚያሣየው ባንድ በኩል ዛሬ በሕይወት ያሉትንና በሌላ በኩል ደግሞ በነፃ ርምጃና ቀይ ሽብር ያለቁትን ወገኖቻችንን ምስልና ስም ዝርዝር ነው። በዚህም መጽሔት ውስጥ አጋጣሚ ሆኖ ጓደኛየና የትግል አጋሬ የነበረው ማርቆስ ሐጎስ የመጽሔት አዘጋጆቹ ከባለቤቱ ጋር ያደረጉትን ቃለ መጠይቅ ለማንበብ በቅቻለሁ። ቃለ ምልልሱን እንዳለ ከማቅረቤ በፊት ከኔ ጋር የነበረውን የትግል ቀረቤታ እንደሚከተለው አቀርበዋለሁ፦

ማርቆስ ሐጎስና እኔ የተዋወቅነው ማኅበራችንን ለሕዝባዊ ሚኒሰቴር አሳውቀን በሕግ ካስመዘገብን በኋላ ነበር። ይኸውም ከታኅሣሥ ፲፱፻፷ ዓ.ም (1960) በኋላ መሆኑ ነው። ከትውውቃችን በኋላም ማርቆስ በሠራተኛው ማኅበር ቀደም ብሎ ሲታገል ስለነበር ጠቃሚ ምክሮችን ይለግሰኝ ነበር። ይኸም ግኑኝነታችን እየጠበቀ ሲሄድ ከአየር መንገድና ቀደም ብሎ ከሚያውቀው ጓደኛው ጋር (ቢስ ኩባንያ ይሠራ የነበርና አሁንም በሕይወት ያለ) አብረን ለመሥራት ተስማማን። እንደሚታወቀው ሁሉ የኢትዮጵያ ሠራተኞች አንድነት ማኅበር( ኢሠአማ) መሪዎቹን በሕጉ መሠረት መርጦ አያውቅም ነበርና ለውጥ እንደሚያስፈልገው ያላንዳች ማመንታት ተስማማን። እኛም በተቻለን መጠን ሐሳባችንን የሚጋሩና የምናውቃቸውን ወንድሞቻችንና እኅቶቻችንን ማነጋገር ጀመረን። በሕጉ መሠረት በየሁለት ዓመቱ መሪዎች መቀየር ስላለባችው እነ ፍሥሐጽዮን ተክሌን አውርደን ከተለያዩ ማኅበራት ተወከለው ከሚመጡት መካከል ለማስመረጥ ነበር ዋናው ዓላማችን። የምርጫው ጊዜ ሰኔ ፲፱፻፷፬ ዓ.ም (1964) ነበርና በተቻለን መጥን አብዛኛውን መሪዎች አነጋግረናል። ነገር ግን ውይይታችን እንዲጠናከር ይረዳን ዘንድ ከቢስ ኩባንያው ወንድማችን ከሣሙኤል ዓለማየሁ ጋር አስተዋወቀን። ሣሙኤል የቢስ ኩባንያ ሠራተኛ

ነበር። የኢሠአማ መሪዎች ማኅበሩን እንደ ርስተ-ጉልታቸው አድርገው ስለሚመለከቱት ምርጫ በተደረገ ቁጥር እነሱኑ መልሰው መላልሰው ይመርጧቸው ነበር። የኛ ቡድን እንዲህ ዓይነቱን አሠራር ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመቀየር ታጥቀን ተነሳን። አምስታችን ከአጋሮቻችንን ጋር ሆነን በወቅቱ በአመራር ላይ የነበሩትን በየነ ሰሎሞንን፤ ፍሥሐ ጽዮንንና የቀረቱን ጓደኞቻቸውን በሠራተኛው ወኪሎች ለመተካት ትግሉን አጧጣፍነው። ከላይ እንደጠቀስኩት ሰኔ ከመድረሱ በፊት ለውጥ የማይፈልጉና ብለውም እያሰናከሉ የነበሩት እንደ ጣምያለው እሸቴንና ብጤዎቹን ጽሕፈት ቤቱ ማደራጀት ጀመረ። በጊዜው የነበሩ የኢሠአማ ባልሥልጣናት የእኛ ጥረትም ሆነ ዓላማ እንዳይሳካ የሠራተኛውን ብዙ ገንዘብ አባክነዋል።

እኛም ደግሞ ከሣሙኤል ጋር ሆነን መደረግ የሚገባቸውን ስልቶችና ዘዴዎች መተለምና ዕቅዶችችን ማውጣት ጀመርን። እንደሚታወቀው ሁሉ ኢሠአማ ከሠራተኛው እሰከ ላብአደሩ ድረስ በርካታ አባላት ነበሩት። በተለይ ደግሞ የኢንዶ-ኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ላብ አደሮች ቁጥር ወደ አራት ሺ ይደርስ ነበር። እንደዚህ ብዙ ሠራተኞችና አባላት ያሏቸው ፋብሪካዎች በምርጫው ጊዜም ወሳኝ ድምፅ ስለሚኖራቸው ሻጥረኛው አመራር ከኛ ኮሚቴ ጋር እንዳይሠሩ ከለከሏቸው፣ እንዳይተባበሩም አደረጓቸው።

ቀኑ ደረሰና ሰኔ ፲፱፻፷፬ ዓ.ም (1964) በኢሠአማ አዳራሽ የሁለት ቀን ስብሰባ ተጠራ። የመጀመሪያው ቀን ማኅበሩ ያደረጋቸውንና የደረሰበትንም ውጣ ውረድ ሲያወያየን ዋለ። በማግሥቱ የምርጫ ቀን ሰለነበር እንደልማዳችው ጽሕፈት ቤቱ የራሱን አስመራጭ ኮሚቴ መድቦ ለቤቱ አቀረበ። ወዲያወኑ የስብሰባው ተካፋዮች የጽሕፈት ቤቱን አሠራር በመቃወም አስመራጭ ኮሚቴ ከቤቱ ውስጥ መመረጥ እንዳለበት አሳሰበ። አመራሩ ግን ፍንከችም አላለም። በዚህ ጊዜ ነበር የቤቱ መንፈስ ቅይርይር ያለው። በአዳራሹ ውስጥ ተወካይ መስለው ነጭ ለባሾች ተኩልኩለው ነበር። ከመካከላችን አንዱ እንዲህ ብሎ ተናገረ፡ “የዝምብ መንጋ ወስከምቢያ አይከፍትም”፤ ተሰብሳቢውም አጨበጨበ። ይሁንና ይህ በእንዲህ እያለ፤ ከትንሽ ዲቃቃዎች ዝምታ በኋላ እሱ ያለው አባባል ሳይሰካ ቀረና ብዙ ከተጨቃጭቅን በኋላ በለስ ቀንቷቸው ሻጥረኞቹ አዳራሹን በቁጥጥራቸው ሥር አደረጉት። የስብሰባው አቅጣጫ ደስ ያላለው ፍሥሓጽዮን ተክኤ ቢሮ ሄዶ ስልክ በመደውል ግማሽ ስዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መንግሥትን ወክለው ዶክተር ሥዩም ተሾመው መጡና ቤቱን በሊቀ መንበርነት እንዲመሩ ተደረገ (ዶክተር ተብየው በአዲስ አበባ ዩኒቨረሰቲ የሲቪክ መምህር ነበሩ)። እሳችውም መንግሥት ቀደም ብሎ አዘጋጅቷቸው ስለነበር መምረጥ ያለባችው እነማን እንደሆኑ ቀደም ብለው ሰለሚያወቁ አሁንም እነ ፍሥሓ ጽዮንና ቡደኖቻቸው ያለምንም ተቃውሞ አስመረጡ። ለዚህም ሥራችው ጃንሆይ መልካም ፈቃዳችው ሆኖ የጎንደር ከተማ ከንቲባ አድረገው ሾሟቸው። ትግሉ ግን አንዴ ሲዳፈን፤ አንዴም ሲጋጋል ቀጥሏል።

የየካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ.ም (1966) አብዮት በፈነዳበት ወቅት ኢሠአማ ከየጠቅላይ ግዛቱ ማለት የማኅበሩ አባለት የነበሩ ሁሉ ወኪሎቻቸውን በመላክ ጠቅላላ ስብሰባ ከየካቲት ፳፭ (25) ቀን አስከ ፳፮ (26) አድርገን; ከማግሥቱ ጀምረን አገር አቀፍ የሥራ ማቆም ጀመርን። ትልቅ ስህተት ያደረገነው መሪዎቻችን እነ ፍሥሓ ጽዮንና ጓዶኞቹ ብቻ እንዲሆኑና ከሠራተኛው ወኪሎቻችንም መካከል የኛ ደጋፊዎች ከሆኑት ውስጥ አንድም ሰው ባለመጨመራችን ጥረታችን ባጭር አንዲቀጭ ተደርጓል። የሥራ ማቆሙን ሐሙስ

ማለት የካቲት ፳፰ ቀን (28) ጀምረን ጥያቄዎቻችን ሳይመለሱ ከሰኞ ጀምሮ በሻጥረኛው ፍሥሓ ጽዮን መሠሪነት ከስብሰባው ወጣ በማለት ለኢትዮጵያ ሬዲዮና ተሌቪዝን ቃል በመስጠት ሠራተኛው ተስማመቷልና ሁሉም ወደ ሥራው እንዲመለስ ሲል ቀጭን ትዕዛዝ አሰተላለፈ። ሠራተኛው ከወኪሎቹ ሳይሰማ ሰኞ መጋቢት ፪ ቀን (2) ወደ ሥራው ተመለሰ። ማኅበራቸውን ወክለው የመጡት ሁሉ አብዛኞቹ በሌላ ቀን ተሰብሰበው ከወስላታዎቹ መሪዎች ጋር የነበረውን ግኑኘነት አቋረጡ። በግልጽና በኅቡዕም ሥራውን ጀመረ።

በዚህም ውለታው ባጭር የተቀጨው የልጅ መኮንን እንዳልካቸው መንግሥት የሕገ መንግሥቱ አርቃቂ ኮሚሽን በተቋቋመት ጊዜ አብሮ ሠራተኛውን ወክሎ አንዲሠራ ተደረገ። ይኽ ዓይነት ንቀት የበለጠውን ቁጣችንን ስለአባባሰው ሁሉንም መሪዎች ተብዮች አሽቀንጥረን ለመጣል ትግሉን አጧጧፍነው። ከዚያማ ማን ያቁመን!

ወደ ፲፱፻፷፯ ዓ.ም(1967) ስንመጣ ደግሞ መስከረም 13 ቀን ኢሠአማ አገር አቀፍ የሥራ ማቆም እያደረገ እያለ ዓለም አብዲና ጓደኞቹ ከደርግ ጋር በምስጢር ተነጋግረው ስለነበር በተለይ ከኢንዶ-ኢትዮጵያ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ መሪዎች፤ በተለይም ደግሞ ጣዕምያለው እሸቴንና መሰሎቹን በመያዝ እነሱን ለሚቃወሟቸው ሳይነገሩ እንዲከሽፍ አድርጓል። ዋናው ዓላማቸው ግን የሥም ዝርዝር አዘጋጅቶ የድርጅት መሪዎችን ለደርግ አሳልፎ በመስጠት ለማሳሰር ነበር። ምኞታቸው ግን በወቅቱ ሳይሳካ ቀርቷል። በዚህ ሻጥር አሠራር ግን ፍሥሓጽዮንና በየነ ሰሎሞን አልተሳተፉም። ቀኑን ባለስታወስም፤ መስከረም/ጥቅምት ፲፱፻፷፯ (1967) ዓ.ም ደርግ አስሯቸው ነበርና እነማርቆስ ሐጎስ ሲፈቱ ማለት በበ፲፱፻፷፰ (1968) ዓ.ም አብረው ተፈተዋል። የሥራ ማቆም አድማውን ዓለም አብዲና ጓደኞቹ ካሰናከሉት ቀን ጀምሮ የማኅበሩ ጽ/ቤት በሠራተኛው ቁጥጥር ሥር እንዲሆን ለማድረግ ክፍተኛ ጥረትና ትግል የተደረገበት ወቅት ነበር። ከግምባር ቀደም መሪዎችና ተሳታፊዎችም ውስጥ አንዱ ***ማርቆስ ሐጎስ*** ነበር። ዓላማችንን ከግቡ ለማድረስም በኢሠአማ አዳራሽና በሌሎች ማኅበራት አዳረሾች እየተሰበሰብን ትግሉን አካሂደናል።

ደርግ ዓለምአቀፉንና የመጀመሪያውን የግንቦት ቀን (May Day 1975) ለማክበር ከምሥራቅ አውሮፓ አገሮች መሪዎችና የማኅበር ተወካዮችን ጋብዞ ነበር። ይህን ከሥራ ላይ ለማዋል ሠርቶ አደሩ እንዲተባበረው በዓለም አብዲ በኩል ጥሪ ተደርጎ ነበር። የደርግ ጥሪ እንደተሰማ ሚያዝያ ፲፰ (18) ቀን ቅዳሜ ኢሠአማ አደራሽ በመስብሰብ ማድረግና አለማደረግ ያለብንን ተነጋግረን ነበር። ዓለም አብዲ የኛን መሰብሰብ በቅድሚያ ስለሚያውቅ ለሥራ ቢሮ ገብቶ ነበር። እሱም ብቻ አይደለም የሱም ደጋፊዎቹ በመካከላችን ነበሩ። ስብሰባው ከተነጋገረባቸው አጀንዳዎችም መኻል ዓለም አብዲን ማገት ነበርና ይዘነው አዳራሹ ውሰጥ በሚገኝ ትንሽ መጋዘን ውስጥ አሰገባነው። ደርግም ወዳጀነቱን ከሱ ጋር በማድረግ ሠረቶ አደሩን ማሰቀየም ቀጠለበት። ለደርግ ባለሥልጣናት ወዳጁ የሆነው ዓለም መታገቱን ያዩ ወዳጆቹ ሰለደወሉላቸው በፍጥነት በምጣት ከነበረበት ጠባብ የዕቃ ቤት ወደ ትልቁ ቢሮው ወሰዱት። የሠራተኛው ወኪሎች ፍላጎት አንድና አንድ ብቻ ነበር። ለብዙ ዘመናት በጉልበትና በሻጥር የያዙትን ሥልጣን ለግምባር ቀደሙ መሪዎች እንዲያሰረክብ እንጂ ዓለምም ሆነ መሰሎቹ እንዲታሰሩ ፍላጎቱም፤ አጀንዳውም አልነበርንም። አሁንም የሠራተኛው ተወካዮች የሠራተኛው ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ

እንዲከበር ከፈለገ ተናጋሪዎቹና አስተባባሪዎቹ ከኛ መካከል (ከሠራተኛው መሪዎች መካከል) ካልሆነ በስተቀር በምንም ዓይነት ተሳታፊ እንደማንሆን ለወኪሎቻቸው በግልጽና በማያሻማ ሁኔታ እምቢኝ፣ አሻፈረኝ አልናቸው። ደርግም ከመጨነቁ የተነሳ ከመዋረድ ብሎ ወኪሎችን ኮሎኔል (ያኔ ሻለቃ) ደሜ(ደምሴ) ዴሬሣንና ኮሎኔል (ያኔ ሻለቃ) እንዳለ ተሰማን ኢሠአማ ጽ/ቤት ድረስ ሚያዝያ ፳፩ ቀን (21) በመላክ ሰብሰቡን አነጋገረዋል። ከብዙ ውይይትና ንትርክ በኋላም ወኪሎቹ ጉዳያችሁንና ብሶታችሁን ከበዓሉ ፍጻሜ በኋላ እንፈተዋለን፣ አሁን ግን የሠርቶ አደሩን ቀን በጋራ እናክበር ሲሉ ቃል ገቡልን። እኛም ተስማምተን በቀጠሩን ቀን ግንቦት ፱ (9) ደርግ ጽ/ቤት እንገናኛለን ስላሉን ተስማምተን ተለያየን።

ይህ በሆነም በሦስተኛው ቀን በዓሉን በዓለም አብዲ ተናጋሪነት በጋለ ስሜት አከበርነው። የቀጠሮው ቀን ደርሶም በማርቆስ መሪነት ወደ ደርግ ቢሮ አመራን። ትንሽ ደቂቃዎች ካቆዩን በኃላ ዘበኛው የቀጠሯችሁ የደርግ አባላት በሥራ ምክንያት ከከተማ ውጭ ስለሄዱ ማነጋገር አትችሉም ሲሉ ገና ከበር መለሱን። እኛም በመጣንበት መንገድ ተመልሰን ወደ ኢሠአማ ጽ/ቤት አመራን። በአንድ የማኅበር መሪ አማካኝነት በአዳራሹ ስብሰባ ሲካሂድ ስለነበር እዚያው ውሰጥ በምትገኝ ቡና ቤት ውስጥ ተሰባሰበን በጥልቅ ከተወያየንበት በኋላ ቤቱ ጽ/ቤቱን በቁጥጥር ሥር እንድናደርግ በአንድ ድምፅ ተስማማን። በዚህም ስምምነታችን መሠረት ከቅዳሜ ግንቦት ፱ ቀን (9) ጀምረን እስከ ሰኞ በሦስት መደብ በመከፋፈል ጽ/ቤቱን መቆጣጠር ጀመርን። ሰኞ ደረሰና ወደ አሥራ አንድ ሰዓት ገደማ ደርግ በኮሎኔል (ያኔ ሻለቃ) ተካ ቱሉ የሚመራ ወታደር ልኮ አዳራሹን አስከበበው። ተካ ቱሉም አሁኑኑ አዳራሹን ለቃችሁ ካልወጣችሁ ባላችሁበት እንጨርሳችሁዋለን እያለ በተደጋገጋሚ ሲያቧርቅብን ማርቆስ ሐጎስ በሰከነ ልሣኑ አዳራሹን ለቀን እንድንወጣና ትግሉን ውጭ ሆነን መቀጠል እንደሚኖረብን ከገለጸልን በኋላ አንድ በአንድ አዳራሹን ለቀን ወጣን። ደርግም በሁለት ስዓቱ ዜና በሬድዮና በተሌቪዥን ኢሠአማ ከዛሬ ቀን ጀምሮ ላልተወሰነ ጊዜ ተዘግቷል ሲል ለሕዝቡ አሳወቀ።

ይህ በእንዲህ እያለ፣ እኛ ከማግሥቱ ጀምሮ በኅቡዕ በመደራጀት የ "ኢሠአማ ትንሣኤ ኮሚቴ" በሚል ሥም ሥራችንን ቀጠልን። እንዲያውም ትግሉ ከምን ጊዜም የበለጠ እንዲጧጧፍ የደርግ እኩይነት በግልጽ የሠራተኛው ጠላት መሆኑን ለአባሎቻችን አረጋገጥልናቸው። ሆኖም ደርግ በየመሥሪያ ቤቱ እየዞረ ማኅበሩ የተዘጋበትን ምክንያት ገለጻ በሚያደርገበት ወቅት ብዙም ሰሚ ስላለገኘ ቅዳሜ ግንቦት ፳፫ ቀን ፲፱፻፷፯ (23, 1967) የገንዘብና የመድኅን ድርጅቶች እንዲሁም አሠሪዎችና ሠራተኞች አንድ ላይ በፓርላማው ውስጥ በተላያዩ አዳራሾች በመሰብሰብ የደርጉ ተወካዮች ሻለቃ ሲሣይ ሀብቴና ኮሎኔል (ያኔ ሻለቃ) ብርሃኑ ባየህ ጽ/ቤቱ ከሰኞ ጀምሮ እንዲከፈት ወስነናል አሉን። አያይዘውም በማግሥቱ መሪዎቻችንን እኛው እራሳችን ከመካከላችን እንደንመረጥ ወኪሎች ከየማኅበሩ ተሰባስብን በኢሠአማ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያውን ሊቀ መንበርና ዋና ጸሐፊ ማርቆስ ሐጎስንና ተሰማ ደሬሳን መርጠናል። እኛም ባደረግነው ድልና ውጤታማ ሥራችን በደስታ መርቅነን በመጣንበት መንገድ ወደ የመኖሪያችን አመራን።

ማርቆስ ሐጎስ ግን ከደርግም በፊት ማለትም በጃንሆይ ዘመን እንዲሁም ኋላ በደርግ ጊዜ የጸጥታው ክፍል አጥብቆ ይከታተለው ነበር። እንዳጋጣሚ ሆኖ ብዙ ጊዜ አዲስ አበባ ከተማ አግኝቸው የማላውቀውን የልጅነት ጓደኛዬና እኔ ሳላውቀው በዚያን ጊዜ ጸጥታ ክፍል የሚሠራ ስለ ማርቆስ ሐጎስ ትውልድ ይጠይቀኛል። ለምን እንደጠየቀኝ ገብቶኛል። ብዙ ጊዜ በፊትም

አሁንም የአባቱ ሥም <<ሐጎስ> የሆነ ከጀብሃና ከሻብያ ጋር ያገናኙት ስለነበር ይህ ሥም በትግርኛ ተናጋሪው ሕዝባችን የተወደደ የሥም መጠሪያ ነው ነግር ግን በሥሙ ብቻ የታችኛው ወይም የላይኛው ትግራይ ይሁን ግን በቀላሉ ለማወቅ አንድ ሰው ሊያውቅ አይችልም ካልተቀራረብክና ግለሰቦቹን ካለወቅህ በስተቀር። ይህ የልጅነት ጓደዬ በተወለድንበት አካባቢና ትምህርት ቤቶች ከሐጎሶች ጋር አብረን እንደተማርን ሳስታውሰው ተገረመና አይ! እውነትክን እኮ ነው እንዲያው ዝም ብሎ መለደፍማ አይቻልም ተባባልንና እንዳንተና እንደኔው ፍጹም ኢትዮጵያዊ እንደሆነና የሠርቶ አደሩም እውነተኛ ጠበቃ መሆኑን አስረግጨለት ተለያየን። ለኔ ወንደሜ ነው ብዙ ቁም ነገሮችን አስተምሮኛልና ከእንግዲህ ወዲያ ባንተ በኩል አትከታተለው፤ ለሌሎቹም ከአንተ ጋር የሚሰሩ ባልደረቦችህም ነገራቸው ተባብልን በመቀላለድ በሠላም ተለያየን። እሱም ራሱ ቢሆን ብዙ ሳይቆይ በ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም (1969) መጨረሻ ላይ ደረግ ጡረታ አስወጣው።

ማርቆስና እኛ ጓደኞቹ ግን ትግሉን ቀጠልን። በእሱም መሪነት መስከረም ፲፰ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም (18, 1968) አገር አቀፍ የሥራ ማቆም አድማ ተጠራና አሁንም ፋሽስቱ ደርግ የስዓት እላፊ አዋጅ አወጀና ተቃውሞው ከሸፈ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ብዙዎቹን የማኅበር መሪዎች ከየሚሠሩበት መሥሪያ ቤት እየተለቀሙ ከሦስት ወር አስከ ሰባት ወር ድረስ ታስረዋል። በግምባር ቀደም ከታሰሩት መሪዎች መካከል አንዱ ማርቆስ ሐጎስ ነበር። የታሠረበትም ቦታ ሌሎቹን ጨምሮ ማይጨው ሠፈር ጃን ሜዳ ከመድረሳችን በፊት በክቡር ዘበኛ ግቢ ውስጥ ነበር። እኔ እንደማስታወስው እሱና ሌሎቹ መሪዎች የተፈቱበት ቀን ዓርብ መጋቢት ፳፭ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም (25, 1968) ነበርና እንዳጋጣሚ ተገኝቼ ሁሉንም ተቀብያቸዋለሁ። ማርቆስና እኔም በዚሁ ቀን ከእስር ቤት ወጥቶ ካገኘሁት በኃላ ትንሽ ቆይቶ በፋሽስቱ ደርግ መገደሉን እስከሰማሁበት ጊዜ ድረስ በተደረገልን የሥራ ክፍፍል ምክንያት አብረን አልሠራንም። መስከረም ፲፪ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ.ም (12, 1969) ደርግን ለማንበርከክ ለሦስተኛ ጊዜ የሥራ ማቆም ሙከራ አድርገን ነበር። በማግሥቱ በኮሎኔል መንግሥቱ (ያኔ ሻለቃ) ላይ የተደረገው የግድያ ሙከራ በሚያሳዝን ሁኔታ ከሸፈ። ነገሮች ሁሉ ተለዋወጡ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነበር የፎቶዎቻችን ዝርዝር በየቦታው እንዲለጠፉ በሌ/ኮሎኔል አጥናፉ አባተ ፊርማ ጥብቅ ምሥጢር በሚል በድፍን ኢትዮጵያ እንዲሰራጭ የተደረገው።

እንግዲህ ዛሬ ይህ በሆነ ከሠላሳ አራት ዓመታት በኃላ በመጽሔቱ የሚከተለውን ታሪኩን ሳነበውና ሥዕሉን ሳየው ብዙ ትዝታዎች ቀሰቀሱበኝና እኔም የየካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ.ም (1966) አብዮት ትዝታ በአዕምሮዬ መጣብኝና የማስታወሰውን ያህል ለወዲፊት የሠራተኛው መሪ ለምትሆኑ ወይም ለታሪክ ተማሪዎች ሊረዳ ይችላል በሚል ይህን የላባደሩን የትግል ታሪክና ገድል ባጭሩ አቅርቢያሁ። በይሕወት ያላችሁት ብዙ ጓደኞቼ ደግሞ በተጨማሪ የምታውቁትን ጨምርመር አድርጋችሁ የሠራተኛውን ቀን እንድትዘክሩት በማክበር አሳስባለሁ። *አበራ ገሙ* የተባለው የመጀመሪያው የማኅበር መሪ ሁሉም ላብአደሮች ጫማ ካላደረጉ እኔ አላደረግም ብሎ አስኪሞት ድረስ በባዶ እግሩ ይሄድ የነበር ጥሩና አስተዋይ መሪ ነበር። እሱንም አብረን እንዘከረው። ማርቆስ ሐጎስ ግን ዛሬ በሕይወት ከሌሉትና የቀይ-ሽብር ሰለባም ከተደረጉት የመምህራን መሪዎች ከዮሐንስ ብርሃኔና ከብርሃኑ እጅጉ እንዲሁም ከሌሎቹ ጓዶቹ ጋር በመሆን ሠረቶ አደሩን ወክሎ ለሠርቶ-አደሩ መብት የተጋደለና ከፋሽስቶችም ጋር ጉረሮ ለጉረሮ ተናንቆ የወደቀ ኢትየጵያዊ አርበኛ ነበር።

# ማርቆስ ሐጎስ <<የሠራተኛው ሠማዕት>

## ከአደራ መጽሔት የተወሰደ

አምባገንን ገዢዎች ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ለሕዝብና ለሕግ የበላይነት የሚታገሉና የሚያታግሉ ግለሰቦች ሁሉ ባላቸው አቅምና ልዩ ልዩ ስልቶች አሰቃይተውና አሳድደው በመግደል ከገጸ ምድር ሲያጠፏቸው ኖረዋል። አምባገነኖች ሁሉ አንድ እስከ መጨረሻው ያልተሳካለችው ነገር ቢኖር የሕዝብን የነፃነት ትግል አሰናከለው ለማስቀረት ያለመቻላቸው ነው። የየትግሉ መነሻ ምክንያት ዓይነትና ደረጃ ቢለይም እያንዳንዱ ትውልድ የየራሱ ጀግኖች ሠማዕታት አሉት፤ ይኖሩታልም።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውሰጥ የሕዝባዊ ገድል ታሪካቸው ያሳለፉት መከራና ስቃይ ተመርምሮ ያልተጻፈ የከፈሉት መሪር መሥዋዕትነት ያልተዘከረ እጅግ ብዙ የሕዝብ ወገን ባለታሪኮች አሉ።

አምባገነን ገዥዎችና ሐሳዊያን የታሪክ ጸሐፊዎች እውነቱን ሁሉ የሐስት ጥላሸት እየቀቡ ቢያድበሰቡስትም የዘመነ ሐቅ ፀሐይ ስትወጣ የጻፉት ሀሰት ሁሉ እንደ ትብያ በንኖ እውነተኛው ታሪክ እንደ በጋ ሌሊት ከዋክብት ይንተገተጋል። ለዚህም ነው ከዛሬ ፴፪ (32) ዓመታት በፊት የፋሽስታዊ ደርግን ኢፍትሐዊ አገዛዝ በቆራጥነት ሲታገሉ ከነበሩት የኢትዮጵያ ሠራተኞች መካከል የኢሠአማ ፕሬዚዳንት የነበረው የማርቆስ ሐጎስ ትግልና የሠማዕታት ታሪክ በአምባገነኖች መቃብር ላይ እንደ ጸደይ አባባ ፈክቶ እንደ በጋ ንጋት ፀሐይ ደምቆ የበራው።

የ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም (1969) መጋቢት ወር ሁለተኛው ሳምንት እንደተጠናቀቀ ፒያሳ ከግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ደቡብ ከፍታው ቦታ ላይ ባለ የቀድሞ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከበተረ ደጀኔ ጋር ሳገኘው ግርማ ሞገሱ ምንኛ ደስ ይል እንደ ነበር ዛሬም ድረስ ይታየኛል። በተገኘበት እንዲያዝ ወይም እንዲገደል የተወሰነበት ፎቶግራፉ በየመሥሪያ ቤቱና በየአደባባዩ የተለጠፈበት ሰው በኀቡዕ መኻል ፒያሳ መገኘቱ ያስገርም ይሆናል። *ቀደም ሲል ታስሮ በነበረበት ወቅት ጀርባና ትክሻው ላይ በደረቅ አኮረማጆና ገላ በሚተለትል አለንጋ ተገርፎ በማንዘሪያ ኤሌክትሪክ ተጠብሶ ሰምበሩ እንደ ገመድ ተጋድሞ የሚታየው ቆዳው እጅግ ሰላመመው ለሕክምና ወደ አዲስ አበባ በኀቡዕ መምጣቱን በትረ አጫወተኝ።* እኔ ሳገኘው ከሕመሙ ድኖ በደህና ሁኔታ ላይ ነበር። በሠራተኛው ማኀበራት ትግል ላይ በስፋት ስለ ምንተዋወቅና በሌላኛው ትግል መስመርም ስለምንገናኝ ሠፊ የመግባቢያ ቋንቋ ነበረን። በወቅቱ እኔም ሥራ ለቅቄ በመንከራተት ላይ ስለነበርኩ የማርቆስን የሞት መርዶ በሬድዮ የሰማሁት ጎጃም በረንዳ አንዲት አልባሌ ሻሂ ቤት ውስጥ ነበር። ዛሬ ከ ፴፪ ዓመታት (32) በኋላ ወደዚያ የሠራተኛ መብት ታጋይ ጀግና ቤት ሄጄ የሕይወት ታሪኩና የጀግና አወዳደቁን ከባለቤቱ ከወይዘሮ አልማዝ ገብሩ ጋር እያወራሁ በእገር ሕሊና ወደነዚያ የመከራ ጊዚያት ነጎደኩ። ከመሪር ትዝታዎቼ መለስ ስለባለቤታችው የሚከተለውን ሐቅ አወጉኝ።

በ፲፱፻፴፭ ዓ.ም (1935) የኢትዮጵያ የምድር ባበቡር ሠራተኞች ማኅበር ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበራትና እውነተኛ መሪዎቻቸው ለላብ አደሩ መብትና የሥራ ነፃነት እጅግ ከፍ ያለ ትግል አካሂደዋል። እውቅ የላብ አደሩ መሪዎችም በመሪር ስቃይ ውስጥ የዘለቀ የሕይወት መሥዋዕትነት ከፍለዋል።

ሚያዝያ ፲፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ.ም (11, 1967) የኢሠአማ ጠቅላላ ጉባኤ ያስተላለፈው ውሳኔ (ገፅ1) <የኢትዮጵያ ሠራተኞች ትግል ብዙ እጅግ በጣም ብዙ ያልተጻፉ ያልታወቁና የተደበቁ ገድሎች አሉት> ይላል። ፋሽስታዊ ደርግን እየታገሉ በክብር ከወደቁት ሠራተኛ ማኅበራት መሪዎች አንዱ የነበረው የኢሠአማ ፕሬዚዳንት የአቶ ማርቆስ ሐጎስ የመሥዋዕትነት ገድል እነሆ!

<አቶ ማርቆስ ሐጎስ በቀድሞው የከፋ ክፍለ ሀገር በየም አውራጃ በ ፲፱፻፴፩ ዓ.ም (1931) ተወለደ። የአንደኛ ደረጃ ትምህርቱን ወሊሶ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ አዲስ አበባ ጄኔራል ዊንጌት አዳሪ ት/ቤት ተማረ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ባጠናቀቀበት ዓመት የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የአስተዳደር ሥራ ሥልጠና ሰጥቶና አወዳድሮ ሠራተኛ መቅጠር ይፈልግ ሰለነበር ማርቆስ ተወዳድሮ አለፈ። በሥልጠናው ወቅት ባሳየው ችሎታ ከተመረጡት አንዱ ሆነና እዚያው ተቀጠረ> አሉ ወይዘሮ አልማዝ ሚች ባለቤታቸው በዓይነ ሕሊና እይታቸው።

<<<ከዚያም ለተወሰኑ ዓመታት አገር ግዛት ሚኒስቴርና (አገር አስተዳደር) አጠር ላለ ጊዜ ደግሞ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሠርቷል። ለምን እንደተመለሰ ባላውቅም እንደገና ወደ ማዘጋጃ ቤት ተመልሶ ነበር። ዳግመኛ ማዘጋጃ ቤትን ለቅቆ ኢምፔሪያል ኢንሹራንስ እንደተቀጠረ ተጋባን። ከዚያም ይኸኛውን ለቅቆ ፓን-አፍሪካን ኢንሹራንስ ገባ። ኢንሹራንስ ይሠራ በነበረበት ጊዜ ነበር ወደ ሠራተኛ ማኅበር የተቀላቀለው። እዚያ ከገባ በኃላ ዕረፍት ብሎ ነገር አልነበረውም። በተለይም የኢሠአማ ፕሬዚዳንት ከሆነ ጀምሮ ሥራ እየበዛበት ሄደ። የሠራተኛው የመብት ጥያቄና ትግል እየተጠናከረ በመምጣቱ መስከረም ፲፱፻፷፰ ዓ.ም (1968) የሥራ ማቆም አድማ ተካሄደ። ያን አድማ ካቀናበሩትና ከመሩት ቀንደኛው አንተነህ ተብሎ ታሰረ። ከሰባት ወራት በኋላ በዓለም ሠራተኞች ድርጅት(ILO) ግፊትና በሠራተኞች የትግል ጫና ተፈታ በእስር ላይ እጅግ ከፍተኛ ስቃይና መከራ ደርሶበታል። ልክ በዓመቱ መጋቢት ፲፯ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ.ም (17, 1969) አንድ ሌላ ከባድ መከራ መጣብን። በተገኘበት እንዲገደል የሚል ትዕዛዝ በመንግሥት በኩል ተሰጥቶ ስለነበር ኑሮና እንቅስቃሴው ሁሉ በጣም አስቸጋሪና በድብቅ ነበር። <የት ውሎ የት እንደሚያድር አናውቅም ነበር> አሉና አንድ አሳዛኝ ትዝታ ፊታቸው ላይ አጠላ። ከአፍታ ዝምታ በኋላ <ከአዲስ አበባ ለመውጣት እንዲያመቸው አስቦ ይመስለኛል ወደ እንጦጦ ኪዳነ ምህረት በሚያስኬደው መንገድ ዳርቻ ላይ ወደሚገኘው ወደ ወላጆቼ ቤት (አባትና እናቴ) ይሄዳል። ውሎ እንኳ አላደረም። ምሽት ላይ ወጥቶ ለመሄድ በመነሳት ላይ ሳለ ምግብ በልተህ ትሄደላህ ብለው ለጥቂት ጊዜ ያቆዮታል።

ማን እንደጠቆመበት አይታወቅም ለካስ የደርግ ወታደሮች ተከታትለውት ኖሯል። ቤታችንን ከበው የአጥሩን በር ያንኳኳሉ። በጣም መሽቷል። ቤታችን መከበቡን እንደተረዳ ወደ ልዩ ልዩ ቦታዎች ሲዘዋወር የሚጠቀምባቸው መታወቂያዎችና ሌሎች በእጁ የነበሩ መረጃዎች ደርግ እጅ እንዳይገቡ የውሀ እንስራ ውስጥ ከተታቸው። የተለያዩ መታወቂያዎች የያዘው በወቅቱ በብዙዎቹ ዘንድ በመልክ ወይም በሥሙ ይታወቅ ስለ ነበር ሥሙን ለመቀያር ታስቦ የተደረገ ይመስለኛል።> አሉ፤ ፊት ለፊት የነበረውን የማርቆስን ፎቶ በኩራት እየተመለከቱ<<<ምን ጊዜም በትግል ላይ ያጋጠመውን ችግርና መከራ ለሌሎች አሳልፎ የማይሰጠው ማርቆስ እቤት የነበሩ ሕፃናት በጓሮ እንዲወጡ ካደረገ በኋላ የከበቡትን ወታደሮች ሊጋፈጥ ተዘጋጀ። አባቴ እኔ በሩን ልከፈት ቢሉት

አይሆንም የምከፍተው እኔ ነኝ አላቸው። በዚህ መኻል ፈንጠር ብለው ቤቱን የከበቡት ወታደሮች አንድ ጥይት ተኮሱ። እሱም በምላሹ አንድ ተኮሰ። ከበው የነበሩት ወታደሮች እቤት ውስጥ ያደፈጠ ተጨማሪ ኃይል ይኖራል ብለው የጠረጠሩ ይመስለኛል ቦታ ለመያዝ አፈገፈጉ። ጨለማ በመሆኑ እነርሱ ሲያፈገፍጉለት እርሱ ሽጉጡን አቀባብሎ ሲጠባበቅ በተከታታይ ተኮሱበት፤ አሱም ወደ እነሱ መተኮሱን ቀጠለ። በመጨረሻ ሁለት ጥይት ብቻ ሲቀረው ተኩሱን አቆመ። ወደ አስፋልት ወጥቶ የድርጅቱን የትግል መዝሙር ዘምሮ መፈክሮችን አሰማ። በመጨረሻም እጄን ለደርግ አልሰጥም ይል ስለነበር አንገቱ ላይ ከማንቁርቱ ከፍ ብሎ በቀኝ የመንጋጋው ሥር ወደ ላይ ተኩሶ በአንዲት ጥይት ራሱን አጠፋ እንጂ ደርጎች አነጣጥረው አልመቱትም። ደርግ የእኔ ወታደሮች ናቸው ተኩሰው የመቱት ብሎ ያስነገረው ፍጹም ሀሰት ነው። ደርግ በተደጋጋሚ በሌሎች ላይ ሲዋሽ እሰማ ነበር። ይኸውም ስለማርቆስ አሟሟት ባስነገረው ዜና ላይ እርሱ ያልሠራበትን መ/ቤት እንደሠራበት መግለጹና ያልፈጸመውን ድርጊት አድርጓል ማለት ነበር> ብለው መጋቢት ፲፰ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ.ም (18, 1969) የወጣውን አዲስ ዘመን ጋዜጣ ከፊል የመጀመሪያ ገጽ ሰጡን። አነበብነው። (እኔ የትግል ጓደኛው የማስታወሰው ግን ማርቆስ እራሱን የገደለው ዓርብ ሌሊት ለቅዳሜ አጥቢያ መጋቢት ፲፯ ቀን (17) እንደ ነበር ነው።) <አዲስ አበባን ከአድኃሪያንና ከቅጥር ነፍሰ ገዳዮች ለማጽዳት በተደረገ አብዮታዊ ምንጠራ በከፍተኛ ፲፩ ቀበሌ ፬ (11 ቀበሌ 4 ) ውስጥ ትናንት ምሽት የቀድሞው የኢሠአማ ኮሚቴ ሊቀ መንበር የነበረው ማርቆስ ሐጎስ በአሳሽ ጓዶች ተገድሏል። ማርቆስ ሐጎስ በመኖሪያ ቤቱ ተደብቆ እጅ አልሰጥም ከማለቱም ሌላ ለፍተሻ በተሰማሩት አሳሽ ጓዶች ላይ ተኩስ በመከፈቱ በተደረገው የተኩስ ልውውጥ ሊገደል መቻሉ ተገልጧል። ...> ይላል። ቀሪውን አርቲቡርቲ ትተነዋል።

<<<ሬሳው አስፋልቱ ላይ ወደቀ። ወታደሮቹ *ቢአር* ጠምደው በመጡበት ጂፕ ላይ አስከሬኑን ጭነው ወደ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ወሰዱት። የ፸ ዓመት (70) ሽማግሌ የነበሩትን አባቴን አቶ ገብሩ አረጋይ ሣህሉንም ወስደው ጃንሜዳ ክቡር ዘበኛ መምሪያ ለሦስት ወር ያህል አሰሯቸው። እናቴን ባይወስዷትም ቅሉ በጣም አንገላቷት። ለአባቴ ስንቅ እንኳ እንዳናቀበል በወቅቱ የት ቦታ እንዳሰሯቸው አናውቅም ነበር። የማርቆስ የክርስትና አባት ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ይሠሩ ስለነበር አስከሬኑን አይተውታል። ሬሳውን እንዲሰጡን ጠይቀን ነበር ነገር ግን አስፈራርተው አባረሩን። ልቅሶና ሐዘን መቀመጥ፤ ሐዘንተኛውን ማጽናናት በተከለከለበት በዚያ የመከራ ዘመን አስከሬን የጠየቅነው እንዲያው ምናልባት እንሞክር በማለት እንጂ ደርግ ይራራል ብለንስ አልነበረም። ቁርጡን ማወቅ ግን ጥሩ ነበር። የት እንደተቀበረ ተከታትለው የነገሩን የክርስትና አባቱ ነበሩ። የተቀበረው ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ጀርባ ደን ውስጥ ነበር። እዚያ መቃብር ቦታ ለሕሊና በሚከብድና እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ በደርግ የተገደሉ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎች ባንድ በጅምላ መቃብር ውስጥ አምስት፣ ስድስት፣ አሥርና ከዚያም በላይ ተደራርበው እንደተቀበሩ መቃብር እየተከፈተ አጽም በተለቀመበት ጊዜ እዚያው ተገኝቼ አይቻለሁ።

ማርቆስ በሞተበት ዕለት የለበሰው እኔ እራሴ በጄ የሠራሁትን ግራጫ ቀለም ያለውን ሹራብ ነበር። መቃብሮቹ እየተቆፈሩ ተራ በተራ ሲከፈቱ የማርቆስን አጽም ለብሷት የነበረውን ሹራብ ለማወቅ እንደምችል ሙሉ እምነት ነበረኝ። እውነትም ያቺ ለብሷት የነበረችው ሹራብ አጽሙን ይዛ ተገኘች። እንዴት ደስ እንዳለኝ መግለጽ ያቅተኛል። በዚያን ጊዜ ወጣቶችና ሌሎቹም በቀይ ሽብር እየተገደሉ ስለነበር ማርቆስ የተቀበረው

ከነሱ ጋር ነው። በቀይ ሽብር የተገደሉ ወጣቶች የተቀበሩትም እዚያው ነበር። የብዙ ወጣቶች ሬሳ ከመቃብር በጅብ እየወጣ ተበልቷል። በዚህም ምክንያት ሲሞቱ በለበሱት ልብስ ምልክት እንደተገኙት ሊገኙ ያልቻሉት በርካቶች ናቸው።

የማርቆስን አጽም ለይተን ካወቅን በኋላ አጥንቱ ተለቅሞ በአዲስ አንሶላ ተጠቀለለ። ከዚያም ከሌሎቹ መሰሎቹ ጋር በመኪና ተወሰደ። ይህ ሁሉ ሲሆን አንዱ ልጄ አብሮኝ ነበር። አቶ ማርቆስ ስንት ልጆች አሉት? አልናቸው ሐሳባቸውን ከመካነ መቃብር ወደ መካነ ሕይወት ለመመለስ። “አምስት ልጆች አሉን። እነሱም ታደሰ፦ ዳዊት፣ አምሳሉ፣ (ሴት) ዘመነና ደጉ ይባላሉ። የመጨረሻው ልጃችን አባቱ ሲሞት የአንድ ዓመት ሕፃን ነበር። ዳዊት ግን ሞቷል ሠራተኛ ነበር። አንዲት ልጅ አለው። እሱን እያሳደግሁ ነው። ሁሉም ራሳቸውን ችለዋል፤ ለቁም ነገር በቅተዋል። በአሁኑ ጊዜ ከኔ ጋር አብሮ የሚኖር የለም። ሁሉም በትምህርት፣ በሥራና በኑሮ የተሳካለቸው፤ በመልካም ሥነ ምግባር ያደጉና የተባረኩ ጥሩ ዜጎች ናቸው። ሳሳድጋቸው አላሰቸገሩኝም።

ስለ አባታቸው የማያውቁት ነገር የለም። ዘርዝሬ ነግሬያቸዋለሁ። በአንድ ወቅት ትልቁን ልጅ የኢሕአፓ ወረቀት በትነሃል ብለው ያዙት። እሱን ሲይዙ እኔ ከሥራ ወደ ቤት በመግባት ላይ ሰለነበርኩ ልቀቁልኝ ብዬ በመጠየቄ ደበደቡኝ። <ደግነቱ ገራፊው በማግሠቱ ለቀቁት።> ብለው በድጋሚው የግፍ ጥቃት ፊታቸው ቅጭም አለ። በመራራው ትዝታ ምክንያት ላፍታ ያህል ዝም አልንና <እስቲ ስለ ቤተሰባዊ ግኑኝነት ይነገሩን> አልናቸው። ይዟቸው ከነጎደው ሐሳብ መለስ አሉና ግርማ ሞገስ የተላበሰ ደርባባ ፈገግታ እያሳዩ <<<ሠራተኛ ማኅበር ውስጥ ከገባ ጀምሮ ልጆቹን ለማየትና ለማጫወት ጊዜ አልነበረውም። የልጆችህን ሕይወት ተመልከት፣ ተከታተላቸው ስለው የስንቱ ድሀ ልጅ እየተንገላታ ያድጋል፣ ይማራል፤ እናትና አባታቸው እየሞቱባቸውም ይኖራሉ። የስንቱን ሠራተኛ ሕይወት መከራ ውስጥ ገብቷል። ልጆቻቸው እየተራቡና የሚለብሱት እያጡ በሚንገላቱበት በአሁኑ ጊዜ እኔ ለራሴ ለልጆቼ የሠራተኛው ትግል በፍጹም አልነጠለነም፣ የእኔ ልጆች ከማን ይበልጣሉ፤ አንቺ ልጆቹን ተከታተይ፤ አሳድጊ፤ ምንም ወስጥ አትግቢ፤ እኔ እንደገባሁበት እወጣዋለሁ ይለኝ ነበር። እኔም አንዲት ፍሬ ሥራ ነበረችኝ። እሱ ከሞተ ልጆቻችንን ማን ያሳድግልናል? እንዴት ሆነው ያድጋሉ? እያልኩ ወደፊት ሰለሚሆነው ሁሉ እጨነቅና እሰጋ ነበር። እሱ ግን ቁርጡን ነግሮኛል። <እግዚአብሔር ይመስገን አደጉ> አሉ ልበ ሙሉነት ባልተበገረ የእናትነት ወኔ።<<እጅግ የሚያሳዝነኝ ግን> አሉ ብስጭት ብለው አንድ ፍትሕና ርትዕ ያጡበትን የመብት ጉዳይ በከፍተኛ ምሬት እያስታወሱ <ምናልባት ጡረታውን ይሰጡኝ እንደሁ ብዬ ጠየቅሁ። ለካስ በየመ/ቤቱ የነበረውን ፋይሉን የደረግ የለወጥ ሐዋርያት ይባሉ የነበሩትን የጊዜው ሹመኞች ልቅም አድርገው አጥፍተውታል። ምን መነሻ ይገኘ ልጀምር? የተሰጠችኝን አንዲት የአየር መንገድ ደብዳቤ ደግሞ የትም አታደረሰኝም። የሚሉት ቢያጡ አስመስክሪ አሉኝ። እኔስ ማን-ነኝና አላስመሰክርም ብዬ ተውኩት። የአገልግሎት ክፍያም ሆነ ጡረታ አላገኘሁም። እርሱ ከከፈለው መሠዋዕትነት ጋር ሲነጻጸር ግን ምንም አይደል። ሌላው የማልዘነጋው ነገር ማርቆስ የሞተ ሌሊት ወታደሮቹ የወላጆቼን ቤት ሲበረብሩ ያገኙትን ገንዘብና ሌላ ቀላል ጠቃሚ ንብረት ሙልጭ አድርገው ወሰዱት።

አንድ ቀን ቤት ስፈትሽ ሻንጣ ሙሉ ዴሞክራሲያ የሚል ወረቀት አግኝቼ እንጀራ ጋገርኩበት። ከተገኘብን ይገድሉናላ! እነዚህን የምታዩዋቸውን የብዙ ማኅበሮች ማኅተም ያለባቸውን ወረቀቶች ያን ጊዜ አግኝቻቸው ቢሆን ኖሮ አልምራቸውም ነበር። ምክንያቱም

እሱ አምስት ልጆች ትቶ ሞቷል። እኔ ከሞትኩባቸው ደግሞ ሜዳ ላይ ፈሰው መቅረታቸው አይደለም ወይ? ብዬ መታሰርም መሞትም አልፈለግሁም። እሱ እንዳይሞትበኝ ብዬ በተደጋጋሚ ተው ብዬው ነበር። እሱ ግን ለሠራተኛው ነፃነት ስል እሞታለሁ፤ እንዲያውም አንቺ ትንሽ ሥራ አለሽ፤ ያላንዳች ገቢ ልጆቻቸውን የሚያሳድጉ የሠራተኛ ሚስቶች አሉ። የኛ ልጆች ከማን ይበልጣሉ ይለኝ ነበር። በዚህ ምክንያት ቅሬታ አድሮብኝ ሁለት ጊዜ ከቤት ወጥቼ ወላጆቼ የአባታቸው እንዳይበቃ ደርግ ልጆቹን ለብሔራዊ ውትድርና እያሳደደ መከራይን አሳየኝ። እኔም የዋዛ አይደለሁም ዘመድና ወዳጅ ቤት ደብቄ እያሳደርኩ ልጆቼንና ወንድሜን አተረፍኩ።> እንዳሉ ድንገት ስሜታቸውን ልውጥ አለና <<ውይ! ውይ!ውይ! ያ ዘመን በዚች አገር ላይ አይደገም> አሉ እየተንገፈገፉ።

አጽሙ ከመቃብር ሲወጣ ምን ተሰማዎት? አልናቸው።<<የደርግን ውድቀት እመኘው ስለነበር አጽሙ ሲወጣ ዳግመኛ የተፈጠርኩ ነው የመሰለኝ። ለኔ ትንሣኤ ነው። ሰው ሁሉ ሲያለቅስ እኔ ዘለላ እምባ ይወረደኛል እንጂ በልቤ የነበረው ደስታ ነበር። እግዚአብሔር ይመስገን ነበር ያልኩት። እንደኔ መከራ የደረሰበት ሁሉ የዚያ አረመኔ መንግሥት ውድቀት በጣም ያስደስተዋል እላለሁ። ለምን ደስ አይለው? ይለዋል እንጂ> አሉና ለዓመታት ባልተንበረከከ ጠንካራ ቅስምና እንድ ንጋት ጎህ በሚያስደስት የእናትነት ፈገግታ። <<ብዙውን ጊዜ ሰው ከሞተ በኋላ ያልሠራውን መልካም ነገር መጨማመር የተለመደ ነው። እኔ ግን እውነቱን ነው የምነግራችሁ። ማርቆስ ደግ ነበር። ሙሉ ደሞዙን ይዞ መጥቶ አያውቅም። ለተቸገሩ የሚሰጥ ሩህሩህ ነበር። ስንቱን ልዘርዝረው። ቤተሰቦቼንም ረድቶ ያቋቋማቸው እሱ ነበር። ልጆቼን ያሳደግሁት ራሴን እረደቼና ታግዬ ነው። ማንም አልረዳኝም። በፊት ትምህርት ሚኒስቴር: ዩኒቨርሰቲ ውሰጥ በጸሐፊነት፤ ጡረታ ከወጣሁ በኃላ ደግሞ የግል ማተሚያ ቤት ሰባት ዓመት ሠርቻለሁ። ኑሮ ባሰቸገረኝ ወቅት በቆሎና ስንዴ ቀላቅዬ እያሰፈጨሁ ልጆቼን አብልቻለሁ። ከልጆቼ ውስጥ ማንም አላሰቸገረኝም። እኔም የማርቆስን አደራ በሚገባ ተወጥቻለሁ።

*<ቤተሰቦቼ ልጆቹን ወስደን እናሰድግ አንቺ ገና ልጅ ነሽ አግብተሽ መኖር ትችያለሽ ብለውኝ ነበር። እኔ ግን ልጆቼን አልሰጥም ሌላም ባል አላገባም ሌላም አልወልድም ብዬ ልጆቼን አሳደግሁ። የሱን አደራ ጠብቄ ልጆቼን በሥነ ሥራዓት በማሳደግና ለቁም ነገር በማብቀቴ ለሀገሬ ብድሬን መልሻለሁ" አሱም ለሠራተኛው ዓላማ ሞቷል። <እኔ ደግሞ ዕድለኛ ነኝ ዓላማዬ ሁሉ ተሳክቷል።> አሉና ውጤታማዋ የቤተሰብ አርበኛ ወይዘሮ አልማዝ ገብሩ በድል አድራጊነት ፈገግታ።>*

# ለመጽሔቱ አዘጋጆች ያለኝ መልዕክት

የቦርድ አባላቱንና የመጽሔቱን አዘጋጆች፦ 1ኛ/ አቶ ደምሴ ጽጌ፤ 2ኛ/ አቶ ኃይለማርያም፤ 3ኛ/ አቶ ታደሰ ማሞ ለቅንብራቸሁ በጣም አመሰግናችኋለሁ። የማርቆስ ሐጎስና የወይዘሮ ዳሯ ነጋሽን ታሪክ እንዲሁም የሠራተኛውን ማኀበር ቀዳማዊ መሪ አበራ ገሙ (እኔ ጫማ አላደረግም ላብ አደሮቼ ጫማ ማድረግ አሰከሚችሉ ድረስ ይል ነበር) አገሬ ብኖር ኖሮ ብዙ ነገሮችን ሰለነሱ እንዲሁም የሌሎቹን ቆራጥ መሪዎች እንደኔ

በይሕወት የሌሉትን መጻፍ እችል ነበር ግን ስደት ላይ ሆንኩና አገሬ መጥቼ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሆነ ከሚያውቋቸውም ጋር ተነጋገሮ ለመጻፍ አልተቻለም።

በአሁን ጊዜ ደግሞ ዕድሜው እየገፋ መጥቷልና ያለን ጊዜ ጥቂት ነው። ሰለዚህ እኛ ባቀናባበረነው አንተ ምን አገባህ እንዳትሉኝ እኔም በበኩሌ አደራ እላችኋለሁ የመጻፍ መብታችሁን አከበረኩ፤ አደነቅሁ አልተጋፈሁም። በጥቂቱም ቢሆን ሳስበውና ስመኘው የነበረውን በከፊል እንድፈጽም አደረጋችሁኝ እንጂ። መልዕክቱ ለብዙዎቹ በተለይ የሠራተኛውን ትግልና መሠዋዕትነት ምን ያህል እንደከፈለበት ለሚቀጥለው ትውልድ እንዲያወቀው በመፈለጌ ጭምር ነው። በዚህ አጋጣሚ ሰለሙዜየሙ መቋቋም/መከፈት በወያኔው/በፀረ-ኢትዮጵያ ዘመን በመሆኑ ግን ቅሬታ አለኝ። ይህ ብቻ አይደለም እነዚህኞቹም ብዙ ማርቆስ ሐጎሶችን በረሃ በነበሩበት ወቀት ከተኙበትና ከሻብያ ጋር በማበር ገድለዋል። አዲስ አበባም እንደገቡ የዩኒቨርሰቲ ተማሪዎችና አሰተማሪዎችን፣ ጥቂት ቆይቶም ደግሞ አሰፋ ማሩን፤ ገ/እግዚአበሔር ኃይሌን (ኝይምን)፤ ተስፋዬ ታደሰን፤ ሽብሬ ደሳለኝን፤ የአሥራ አምስትና የአሥር ዓመቱን ሕፃን፤ ሰኔ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም (1997ና) ኅዳር ፲፱፻፺፰ ዓ.ም (1998) ደግሞ ከሁለት መቶ በላይ የተገደሉት ከዚያም አልፎ ድፍን አገራችንን ከተቆጣጠሩ በኃላም ደግሞ በየጠቅላይ ግዛቱ የገደላቸው፤ የጨረሷቸው፤ በሳት ያቃጠሏቸው፤ ገደል የወረወሯቸው ሥማችው በሙዩዜይሙ የሚመመዘገበት ቀን ሩቅ አይሆንም።

ይህ የዛሬው ጽሁፌ ግን ከናንተ መጽሔት ከወሰድኩት ድንቅና ታሪካዊ የሆነ ቃለ-መጠይቅ ጋር ተቀናብሮ ዘንድሮ ለምናከብረው የዓለም ሠራተኞች ቀን (ሜይ-ዴይ) ለወደቁት ሠማዕታት በመታሰቢያነት እንዲሁም አብዮቱ የፈነዳበትን ፴፯ኛ ዓመት (37) ለማክበር እንዲወጣ አደርጋለሁ።

## ድል ለሕዝባችን!!